የካቲት 9 ቀን 2004 ዓ/ም

Feb. 17/2012

*"ወነአምን በአሐቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፤*

*በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን።"*

## በኢትዮጵያና በውጭ ሀገር የምንገኝ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልዑካን አበው ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሰላምና አንድነት ተገናኝተን ከተወያየን በኋላ የተሰጠ

## የጋራ መግለጫ።

ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት ከኢትዮጵያና በውጭ ሀገር ከሚኖሩት አባቶች የተላከን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላም ልዑካን ከየካቲት 4-9 ቀን 2004 ዓ.ም (Feb. 13-17/ 2012) በአሪዞና ክፍለ ግዛት በፊኒክስ ከተማ በ 2310 East Highland Hotel Phoenix, Arizona በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና አንድነት ጉባኤ አማካይነት የዕርቀ ሰላም ውይይት ለሁለተኛ ጊዜ አካሒደናል።

ለብዙ ዓመታት ሲጠበቅ የነበረው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና የአንድነት ጉባኤ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን የአንድነት ቀን መቃረብ አብስሮአል። ልዑካኑ የጋራ አጀንዳችንን በጉባኤው አማካይነት ከአዘጋጀን በኋላ የካቲት 7 ቀን 2004 ዓ.ም ከ20 የመለያየት ዓመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ፊት ለፊት ተቀምጠን ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት በስፋት ተነጋግረናል።

የተነጋገርንባቸው የመወያያ አጀንዳዎችም ቀኖና ቤተ ክርስቲያንንና ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን የሚመለከቱ ናቸው። የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ለመመለስ ዕርቀ ሰላሙ መከናወን እንደሚገባው ተስማምተናል። ይሁን እንጂ በጋራ ውይይታችን ላይ የሐሳብ ልዩነት ታይቷል።

ቀደም ሲል የሰላምና አንድነት ጉባኤ ባወጣውና ልዑካኑ በተስማማንበት ባለ አምስት ነጥቦች የመወያያ መመሪያ መሠረት የመፍትሔ ሐሳብ አቅርበናል። ሁለቱም ልዑካን ባቀረብናቸው የመፍትሔ ሐሳቦችም ልዩነት በመታየቱ የሰላምና አንድነት ጉባኤው ሁለቱን ያስማማል ያለውን የመፍትሔ ሐሳብ አቅርቧል። ከዚያም የሰላምና አንድነት ጉባኤው ባቀረባቸው የመፍትሔ ሐሳቦች ላይ ከተነጋገርንበት በኋላ ጉዳዩን ጊዜ ወስዶ በጥልቀት ማጥናት እንደሚያስፈልግ በመግለጥ ለሚቀጥለው ጉባኤ የደረስንበትን ውጤት ለማቅረብ ተስማምተናል።

ስለሆነም የዕርቀ ሰላሙ ውይይት በጽኑ መሠረት ላይ የተጣለ በመሆኑ የቤተ ክርስቲያናችን ሰላምና አንድነት እስኪረጋገጥ ድረስ እንዲቀጥል ተስማምተናል። በመሆኑም ሦስተኛው የሰላምና አንድነት ጉባኤ በሐምሌ ወር 2004 ዓ.ም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና አንድነት ጉባኤ በሚያመቻቸው ቀንና ቦታ እንዲካሔድ ተስማምተን ወስነናል።

በመጨረሻም ጉባኤው የቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት ከሁሉ በላይ በመሆኑ፤

1ኛ/ በኢትዮጵያም ሆነ በውጭ ሀገር የሚኖሩ አባቶች ለሰላሙ እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን ሁሉ በቃልም ሆነ በጽሑፍ እንዲሁም በተግባር ከመፈጸም መታቀብ እንደሚያስፈልግ፤

2ኛ/ ስለ አንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አንድነትና ሰላም በሀገራችን ኢትዮጵያም ሆነ በመላው ዓለም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ተግተው እንዲጸልዩ፤

3ኛ/ የዚህ መድረክ አመቻች የሆነውን የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የሰላምና አንድነት ጉባኤ በሚያስፈልገው ሁሉ እንዲተባበሩ እናሳስባለን።

በመጨረሻም በፊኒክስ፤ በአሪዞና የሚገኙትንና ለሁለተኛው ጉባኤ አበው መሳካት የተባበሩትን ካህናትና ምእመናንን ሁሉ ከልብ እናመሰግናለን።

**የሰላም አምላክ ክርስቶስ ሰላሙን ያጽናልን!**

<u>የሰላም ልዑካኑ ሙሉ ስምና ፊርማ</u>

<u>ከኢትዮጵያ</u>

1ኛ/ ብፁዕ አቡነ ገሪማ (ዶ/ር) የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት፣ የውጭ ግኙኝነት የበላይ ኃላፊ፣ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፐሬዝዳንትና የዓለም ሃይማኖቶች ምክር ቤት ለሰላም የክብር ፐሬዝዳንት ቢሮ ዋና ጸሐፊ፣ የድሬዳዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ________________

2ኛ/ ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ የደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ________________

3ኛ/ ንቡረ እድ ኤልያስ አብርሃ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ምክትል ሥራ አስኪአጅና የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ዋና ሥራ አስኪያጅ ________________

<u>ከሰሜን አሜሪካና ከአውሮፓ</u>

1ኛ/ ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ________________

2ኛ/ ብፁዕ አቡነ ኤልያስ የአውሮፓና የምሥራቅ አፍሪካ ሊቀ ጳጳስና የውጭ ግንኙነት መምሪያ ክፍል ኃላፊ ________________

3ኛ/ መልአከ ገነት ገዛኸኝ ገብረ ክርስቶስ በሰሜን አሜሪካ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ሥራ አስኪያጅና የቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት ምክትል ጸሐፊ ________________

4ኛ/ ሊቀ ካህናት ምሳሌ እንግዳ በካናዳ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ዋና አስተዳዳሪና የቅዱስ ሲኖዶስ የውጭ ግንኙነት ክፍል ኃላፊ ________________